

# መግባት ሙአለ ህፃናት

## የትምህርቲ ቤት ዝግጁነት መመርያ ለ ቤተሰብ

Fairfax County
OFC Office for Children

**ለጎረቤት እና ለማሕበረሰብ ኣገልግሎቶች • የህፃናት ፅሕፈት ቤት**

12011 Government Center Parkway, Suite 920

Fairfax, Virginia 22035-1102

**ስልክ ቁጥር፦** 703-324-8000

**www.fairfaxcounty.gov/OFC**

Fairfax County
Neighborhood and Community Services

**የፌርፎክስ ኣዉራጃ፣** VA
**ሕትመት። የታተመበት ቀን፡** 5/2022

**የፌርፎክስ ኣዉራጃ ለሁሉም ዜጎች እና እንቅስቃሴዎች እኩል የሆነ ተደራሽነት ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው።** የTTY **ቁጥር ካልተጠቀሰ** 711/**የቨርጂንያ የእርዳታ መስመር ይጠቀሙ። በተጠየቀ ግዜ በቂ የሆነ መስተንግዶ ይደረጋል፡ ወደ** 703-324-8000 **ይደዉሉ።**

# መግባት
# ሙኣለ ህፃናት

የትምህርቲ ቤት ዝግጁነት መመርያ ለ ቤተሰብ



# ወደ ሙአለ ህፃናት መግባት!

ሴፕተምበር 30 ላይ ልጅዎ 5 ዓመት የሚሞላው ከሆነ በቅርቡ ሙአለ ህፃናት የሚጀምሩ ይሆናል።

ይህ መመርያ ልጅዎ ወደ ሙአለ ህፃናት ከሚገባበት ዓመት በፊት “ወደ ሙአለ ህፃናት ለመግባት” ዝግጁ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ምን መስራት እንዳለባቹ የተወሰኑ ሀሳቦች ይሰጣቸዋል።

መመርያዉ ልጅዎ ለሙአለ ህፃናት በትክክል እንዲመዘገብ ሊወስዷቸዉ የሚገቡ ደረጃዎችንም ይዞአል።

በመጨረሻ የልጅዎን የሙአለ ህፃናት ዝግጁነት ክህሎት እንዲያድግ ለመርዳት ስለ ትምህርት ቤት እና ማሕበረሰብ መርጃዎች መረጃ ኣለዉ።



# ማውጫ


እርስዎ የምስሉ አስፈላጊ አካል ነዎት ........................................ 4

ጥሩ ተግባቦት ቤት ዉስጥ ይጀምራል............................................ 4

ልጅዎ ለሙአለ ህፃናት ዝግጁ እንዲሆን የሚረዱ የተለመዱ ዘዴዎች.......................... 5

ከሌሎች ጋር መግባባት....................................................... 6

ጤናማ አካላት እና አእምሮዎች መገንባት........................................ 7

የትምህርት ቤት ዝግጁነት ተሞክሮዎች ወቅታዊ የቀን መቁጠሪያ ..................... 8-11

ወደ ሙአለ ህፃናት መሸጋገር.................................................. 12

ከማህበረሰብ መርጃዎች ጋር መገናኘት ........................................ 13

ጠቃሚ መርጃዎች ለቤተሰብ................................................... 14

ሕትመቶች.................................................................. 14

ድህረ ገጾች..................................................................14

ቪድዮዎች .................................................................. 15

መተግበርያዎች ............................................................. 15

# እርስዎ የምስሉ አስፈላጊ አካል ነዎት

## ጥሩ ተግባቦት ቤት ዉስጥ ይጀምራል

በሙአለ ህፃናት ውስጥ ልጅዎ ቀኑን ሙሉ ከሌሎች ጋር ይነጋገራል። ልጅዎ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል:

- ፍላጎቶቻቸውን እና መሻቶቻቸውን ማሳወቅ።
- የተለያዩ ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ነገሮችን እና ዝግጅቶችን መግለፅ።
- ቀኑ ላይ ወይም ከዛ በፊት የተከሰቱ ነገሮችን ማካፈል።
- በጋራ ጨዋታ ላይ መሳተፍ።

እርስዎ እና ልጅዎ በአገርዎ ቋንቋ ሲናገሩ የተግባቦት ክህሎቶችን እየገነቡ ነው።

- እናንተ ስለምትሰሩትና እነሱ ስለሚሰሩት ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ጨዋታ ላይ ወይም ከጓደኛቸዉ ጋር ሲጎበኙ ምን እንደተፈጠረ ይጠይቋቸዉ።
- መጀመርያ ላይ፣ ቀጥሎ ከዛ ደሞ መጨረሻ ላይ ምን እንደተፈጠረ ይጠይቁ።
- ነገሮችን እና ተግባሮችን የሚገልፁ ዝርዝሮችንም እንዲያካትት ልጅዎን ይጠይቁ።
- ቀላል ኣቅጣጫዎችን እንዲከተል ልጅዎን ይጠይቁ።
- ቀጥሎ ምን እንደሚከሰት እንዲገምት ልጅዎን ይጠይቁ።



## ልጅዎ ለሙአለ ህፃናት ዝግጁ እንዲሆን የሚረዱ የተለመዱ ዘዴዎች

በቤት ውስጥ የተለመዱ ዘዴዎች መኖሩ ልጅዎ በመዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ያሉትን ልምዶች እንዲከተል ለማዘጋጀት ይረዳል።

- መደበኛ የጥዋት መርሀ ግብር ያዘጋጁ (መነሳት፣ መልበስ፣ መብላት፣ ወደ አፀደ ህፃናት መሄድ ወይም የቀኑ ፕላን ማዉጣት)።
- ቁርስ የጠዋቱ የተለመደ ተግባር አንዱ አካል መሆኑን ያረጋግጡ።
- በተመሳሳይ ሰዓት የምግብ እና የመክሰስ ሰዓት ይኑራቹ።
- ለአካላዊ እንቅስቃሴዎች ያቅዱ።
- የስክሪን ሰዓት የሚፈቀድበትን ጊዜ መርሐግብር ያውጡ።
- ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ማሸጋገርያ ያቅዱ።
- ለቀጣዩ ቀን አቅርቦቶችን ያዘጋጁ።
- በየቀኑ ለማንበብ የግዜ ፕሮግራም ያዉጡ።
- መደበኛ የመኝታ ጊዜን ያዘጋጁ።




## ከሌሎች ጋር መግባባት

ከሌሎች ጋር መግባባት ወደ ሙአለ ህፃናት  የሚደረገውን ሽግግር ለልጆች ቀላል የሚያደርግ ክህሎት ነው።

ከሌሎች ጋር መግባባት የሚችሉ ልጆች የሚከተሉትን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ያውቃሉ፡ -

- ከሌሎች ህፃናት እና ከወጣቶች ጋር እንዴት ግዜ ማሳለፍ እንዳለባቸዉ።
- በሕብረት መጫወት እና እንዴት ተራቸዉን እንደሚጠብቁ።
- አሻንጉሊት መጋራት።
- ችግሮችን እንዴት በቃል እንደሚፈቱ።
- ሰዎችን እና ንብረትን እንዴት ማክበር እንዳለባቸዉ።
- እንዴት እርዳታ እንደሚጠይቁ።
- ጓደኞችን እንዴት ማፍራት እንዳለባቸዉ።
- ስለ ስሜቶቻቸዉ እንዴት ማውራት እንዳለባቸዉ።
- እንደ እባክህ፣ ኣመሰግናለሁ፣ ይቅርታ አድርግልኝ፣ አዝናለሁ፣ እርዳታ እፈልጋለሁ እና መሞከር እችላለሁ ያሉ ቃላትን ይጠቀሙ።
- ቀላል ኣቅጣጫዎችን ይከተሉ።
- ከእርስዎ እና ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ይለዩ።



# ጤናማ አካላቶችን እና አእምሮችን መገንባት።



## እንቅልፍ

ልጅዎ በቂ እንቅልፍ እያገኘ እንዳለ ለማረጋገጥ መደበኛ የመኝታ ግዜን ያዘጋጁ። አብዛኞዎቹ ጨቅላ ህፃናት ከ 10 እስከ 13 የእንቅልፍ ሰዓታት ይፈልጋሉ። ልጅዎ በሙአለ ህፃናት ውስጥ የአጭር እንቅልፍ ጊዜ አይኖረውም።

## እንቅስቃሴ

መደበኛ የአካል እንቅስቃሴ የቤተሰብዎ የተለመደ ተግባር አካል ያድርጉት። እንደ መሮጥ፣ ወደ ዛፍ መውጣት፣ መወርወር፣ መዝለል፣ ኳስ መምታት፣ በአንድ እግር ሚዛን መጠበቅ፣ ዥዋዥዌ መጫወት ያሉ እንቅስቃሴዎችን የሚያበረታቱ ጨዋታዎችን ይጫወቱ።

## ጥሩ አመጋገብ

ጤናማ መክሰስ እና ምግቦች ሲሰሩ ልጅዎ እንዲረዳዎት ያድርጉ። ልጅዎ በየሳምንቱ አዲስ ምግብ ለመብላት እንዲመርጥ ያበረታቱት። ሙአለ ህፃናት ላይ ልጅዎ የራሱን ምሳ ከቤቱ ማምጣት ይችላል ወይም ካፌዉ ላይ የራሱን ምርጫ ሊወስድ ይችላል።

## የስክሪን ግዜ

ስክሪኑ (ኮምፒተር፣ አይ ፓድ፣ ቴሌቪዥን) ላይ ስለሚያዩት ነገር ይነጋገሩ። በተለይ ከመኝታ ሰዓት በፊት የስክሪን ግዜ ገደብ ያዘጋጁ።

## ስሜታዊ እድገት እና ራስን መቆጣጠር

ስለ ህጎች እና ዉጤቶች ይወያዩ እና ይስማሙ። ልጅዎን ጥፋት ማጥፋት የመማር አንድ አካል መሆኑን እንዲረዳ ያግዙ። ከባድ ቢሆንም ሙከራቸዉን እንዲቀጥሉ ያበረታቱዋቸዉ። ልጅዎ ለአንድ ችግር ብዙ መፍትሄዎችን እንዲፈልግ ያበረታቱት። እንዲያቅዱ፣ እንዲያተኩሩ እና እንዲያስታዉሱ አግዟቸዉ።

# የትምህርት ቤት ዝግጁነት ተሞክሮዎች
# ወቅታዊ የቀን መቁጠሪያ

ስለ ልጅዎ እድገት ስጋት ካለዎት ወደ ፌርፋክስ አዉራጃ ህዝባዊ ቅድመ ልጅነት መለየት እና አገልግሎቶች በ 571-423-4121 ይደውሉ። ስለ ጣልቃ ገብነት፣ የስራ ቦታዎች፣ ማጣራት እና ግምገማ መረጃ ይሰጥዎታል። እነዚህ "Child Find" አገልግሎቶች ከ20 ወር እስከ አምስት ዓመት ለሆኑ ህጻናት ነዉ የሚሰጠዉ።

**ለጸደይ የሚሆኑ አንዳንድ አሪፍ መጽሀፍቶች፡**

"A is for Autumn" በ Robert Maass

"Leaf Man" በ Lois Ehlert

"It's Fall!" በ Linda Glaser

"Sixteen Runaway Pumpkins" በ Dianne Ochiltree

"Dappled Apples" በ Jan Carr

"Turkey Trouble" በ Wendi Silvano

## ዓመቱን በሙሉ

- መዝሙሮችን ይዘምሩ እና ታሪኮችን ይንገሩ እና ደግመዉ ይንገሩ።
- መጽሀፍቶችን ያንብቡ። ምን እየተከናወነ እንዳለ ይወያዩ።
- በልጅዎ ስም ያሉ ፊደሎችን ይመልከቱ።
- ልጅዎ ተመሳሳይ በሆነ ድምጽ የሚጣመሩ ወይም የሚጀምሩ ቃላትን እንዲያስተውል ይርዱት።
- እንቆቅልሾች ላይ ይስሩ።
- ቀላል የሰሌዳ ጨዋታዎችን ይጫወቱ።
- ስዕሎችን ለመሳል ማርከሮችን፣ ባለ ቀለም እርሳስ እና እርሳሶችን ይጠቀሙ።
- የመቀስ አጠቃቀሞችን ይለማመዱ።
- ጨዋታዎችን መደርደር እና መቁጠርን ይጫወቱ።
- ቁጥሮችን ይጠቀሙ እና ይቁጠሩ።
- ልጅዎ ነገሮችን ሲገልፅ የቀለም፣ የቅርፅ እና የመጠን ቃላትን እንዲጠቀም ያበረታቱት።
- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጨዋታዎችን ይጫወቱ።
- ልጅዎ በጸጥታ መቆም ወይም መቀመጥ ያለበት ጨዋታዎችን ይጫወቱ።
- ቤተ መጻህፍቱን በመደበኛነት ይጎብኙ። ልጅዎ መፅሀፍት እንዲመርጥ ይርዱት።
- ልጅዎ ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ ያበረታቱት።

## ጸደይ (መስከረም_ህዳር)

- የጸደይ ምልክቶችን ለማየት በቤተሰብ አንድ ላይ የእግር ጉዞ ያድርጉ።
- ለውዝ የሚቀብሩ ሽኮኮዎች፣ ዝይዎች ከአናት በላይ እየበረሩ እና ቀለማቸውን የሚቀይሩትን ቅጠሎች ይፈልጉ። የአየር ሁኔታ ላይ ስላሉ ለዉጦች ይናገሩ።
- ልጅዎን ኮቱን መልበስ እና ማዉለቅ እንዲሁም መቆለፍ እና/ወይም ዚፕ መዝጋት እንዲችል ያስተምሩት።



## በጋ (ዲሰምበር_ፌብሯሪ)

### የሙአለ ህፃናት ምዝገባ

- ልጅዎ ለሙአለ ህፃናት የት እንደሚመዘገብ ለመወሰን የፌርፋክስ ኣዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች የወሰን መረጃ ስርዓት http://boundary.fcps.edu/boundary ላይ ይጠቀሙ።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቱን ይጎብኙ።
- ልጅዎን ሙአለ ህፃናት ላይ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች መሰብሰብ ይጀምሩ። እነዚህ የኗሪነት ማረጋገጫ፣ የልደት የምስክር ወረቀት፣ የጤና እና የክትባት መዝገቦችን ያካትታሉ። የምዝገባ ሂደቶች እና ቅጾች www.fcps.edu ላይ ይገኛሉ ወይም ከማንኛዉም የፌርፋክስ ኣዉራጃ ኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምዝገባ ፓኬት መዉሰድ ይችላሉ።
- ለማንኛዉም የሙአለ ህፃናት ምዝገባ ቀን እና መምርያ የሚሰጥበት ዝግጅት ለማወቅ በአካባቢዎ የሚገኘውን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።
- በማህበረሰብዎ ውስጥ በሙአለ ህፃናት ዝግጁነት አውደ ጥናት ላይ ለመሳተፍ እቅድ ይያዙ።
- “ወደ ሙአለ ህፃናት መሻገር” ዝግጅት ለቤተሰብ የታቀደ መሆኑን ለማወቅ የቅድመ ልጅነት ትምህርት ፕሮግራሞችዎን ያነጋግሩ።
- ከትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ እንክብካቤ ከፈለጉ የፌርፋክስ ኣዉራጃ የትምህርት ዕድሜ የህፃናት እንክብካቤን (FairfaxCounty.gov Search: SACC) ያነጋግሩ ወይም የህፃናት ቤት ፅሕፈቱን “Child Care Search” መሳርያን ይጠቀሙ።

**ለበጋ የሚሆኑ አንዳንድ ኣሪፍ መጽሀፍቶች፡**

“How to Build a Snow Bear” በ Eric Pinder

“Over and Under the Snow” በ Kate Messner

“The Snow Dancer” በ Addie K. Boswell

“Snowballs” በ Lois Ehlert

“The Snowy Day” በ Ezra Jack Keats

### ከልጅዎ ጋር እንቅስቃሴዎች

- ይሰብሰቡ እና ከቤት ውጭ የተወሰነ የቤተሰብ ጊዜ ያሳልፉ።
- ልጅዎ ኣካባቢው ላይ ስላያቸዉ ለዉጦች ይነጋገሩ። ቅጠሎቻቸውን ያረገፉ እና አሁንም አረንጓዴ የሆኑትን ዛፎች ይመልከቱ። የቤሪ ፍሬዎችን እና ጥድ ኮኖችን ይፈልጉ።
- በጋራ መጽሐፍ ለመጋራት በየቀኑ ጊዜ ፈልጉ። ስለ ክረምት ታሪኮች የያዙ መጽሃፎችን ይጋሩ። ስላነበቧቸው ተወዳጅ ታሪኮች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።



## በልግ (ማርች_ሜይ)

**የሙአለ ህፃናት ምዝገባ**

- ከእርስዎ የሕፃናት ሐኪም ወይም የጤና ክሊኒክ ጋር ቀጠሮ ይያዙ።
- ሁሉንም የምዝገባ ወረቀት ጨርሰው ወደ አካባቢዎ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይመልሱ።
- በአጎራባችዎ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በታቀዱት የሙአለ ህፃናት መመርያ መርሃ ግብሮች ላይ ይሳተፉ።
- የቅድመ ልጅነት ፕሮግራም ልጅዎ ከሚማርበት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር መረጃ እንዲያካፍል ለማስቻል የመረጃ ልውውጥ ቅጽ ይፈርሙ።
- ልጅዎ የሚማርበትን ትምህርት ቤት የፌስቡክ ገጽ "Like" ወይም "Follow" ያድርጉ። ትምህርት ቤቱን በትዊተር ይከተሉት።
- ከትምህርት ቤቱ በየግዜዉ ወቅታዊ የሆነ የፈለጉትን የፌርፋክስ አዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ዜና ለማግኘት ይመዝገቡ። ለደንበኝነት የFCPS Subscriber Preferences Page (ተመዝጋቢ ምርጫዎች ገጽን) ይጎብኙ እና የኢሜይል አድራሻ ያቅርቡ። ርእስ ይምረጡ። ELEMENTARY SCHOOLS ን ይምረጡ። ትምህርት ቤት ይምረጡ።

**ለበልግ የሚሆኑ አንዳንድ አሪፍ መጽሀፍቶች፡**

"It's Spring!" በ Linda Glaser

"UnderGROUND" በ Denise Fleming

"In the Garden with Dr. Carver" በ Susan Grigsby

"So Many Circles, So Many Squares" በ Tana Hoban

"Rosie's Walk" በ Pat Hutchins

"Planting a Rainbow" by Lois Ehlert

**ከልጅዎ ጋር የሚያደርጉት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ሙአለ ህፃናት ማዉራት ይጀምሩ።
- የሙአለ ህፃናትን መጀመር በተመለከተ መጽሃፎችን እንዲጠቁም የቤተ-መጻህፍት ባለሙያውን ይጠይቁ።
- ከልጅዎ ጋር ትምህርት ቤቱን ለመጎብኘት ቀጠሮ ማስያዝ እና የሙአለ ህፃናት ክፍልን መጎብኘት ይችሉ እንደሆነ ያስቡ።
- የትምህርት ቤቱን መጫወቻ ሜዳ ይጎብኙ።
- አንድ ሰው ልጅዎን የአዉቶብሱን ዉስጥ እንዲያይ ይፈቅድለት እንደሆነ ይመልከቱ።
- እንደ የእሳት አደጋ ወይም ፖሊስ ጣብያ፣ የፖስታ ፅሕፈት ቤት ወይም የገበሬዎችን ገበያ ያሉ በማሕበረሰባቹ የሚገኙ ቦታዎችን ይጎብኙ።
- ከልጅዎ ጋር የሚገዙ የግሮሰሪ ዝርዝር ያዘጋጁ። እነዚህን እቃዎች በመደብሩ ውስጥ ያግኙዋቸዉ።



## ክረምት (ጁን - ኦገስት)

ወደ ሙአለ ህፃናት መሸጋገር

- ወደ ትምህርት ቤቱ ልጅዎን የሚያስተዋዉቅ ደብዳቤ ይፃፉ።
- የትምህርት ቤቱን ድህረ-ገጽ እየደጋገሙ ይጎብኙ እና ስለ “ወደ ትምህርት ቤት መመለስ” ዝግጅቶች መረጃ ለማግኘት ይመልከቱ።
- ክረምቱን ሙሉ የልጅዎን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይጎብኙ።
- ተመሳሳይ ትምህርትቤት ላይ ከሙኢ.ማሩ ልጆች ጋር የጨዋታ ግዜ ለማሳለፍ እቅድ ያዉጡ።
- እንደ የጀርባ ቦርሳ እና የቤተ መፃህፍቱ መጽሀፍቶች ያሉ የልጅዎን የመዋዕለ ሕፃናት አቅርቦቶች የሚያስቀምጡበት ቦታ ቤት ዉስጥ ይምረጡ።

ከልጅዎ ጋር የሚያደርጉት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች

- ልጅዎ ሙሉ ስሙን እና ሲፃፍ ምን እንደሚመስል ማወቅ አለበት። በቅፅል ስም ወይ በሌላ ስም የሚታወቁ ከሆነ የትዉልድ ስማቸዉንም ማወቅ አለባቸዉ።
- ልጅዎ በራሱ እንዲበላ ያለማምዱት (የጁስ ሳጥኖችን መክፈት ወዘተ)።
- ለመልበስ እና ለማዉለቅ ቀላል የሆኑ ልብሶች ይግዙ።
- በእግረኛ መንገድ እና ያለ ትልቅ ሰዉ መንገድ አለመሻገርን ያሉ የደህንነት ደንቦችን ይገምግሙ።

**ለክረምት የሚሆኑ አንዳንድ አሪፍ መጽሀፍቶች:**

“Beetle Bop” በ Denise Fleming

“The Kissing Hand” በ Audrey Penn

“One, Two Grandma Loves You” በ Shelly Becker

“Yoko Writes her Name” በ Rosemary Wells

“Actual Size” በ Steve Jenkins

“How Do Dinosaurs Go to School?” በ Jane Yolen

“School Bus” በ Donald Crews

“Countdown to Kindergarten” በ Alison McGhee



# ወደ ሙአለ ህፃናት መሸጋገር

እያንዳንዱ የሙአለ ህፃናት ክፍል የተለየ ነው ነገር ግን ሁሉም የሙአለ ህፃናት ክፍሎች ልጆች በቀን ውስጥ በሙሉ ቡድን፣ በትንሽ ቡድን እና በግለሰብ የትምህርት ልምዶች ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳሉ። በቀኝ በኩል የሙአለ ህፃናት መርሃ ግብር ናሙና ተዘጋጅቷል።

ልጆች የሚከተሉትን የሚያሟሉ ከሆኑ ወደ ሙአለ ህፃናት በቀላሉ ይሸጋገራሉ፡

- ችግር ፈቺ ከሆኑ።
- አዲስ አካባቢዎች የሚመቻቸዉ ከሆነ።
- ውሳኔ ሰጪዎች ከሆኑ።
- ጉጉ ከሆኑ።
- ሁሉንም ነገር ሞካሪዎች ከሆኑ።
- ጎበዝ ተግባቢዎች ከሆኑ።

| ግዜ (በደቂቃዎች) | የቀን ክፍል |
|---|---|
| 10-15 | መድረስ/ቁርስ/ቡድን መፍጠር |
| 20 | የጠዋት ስብሰባ |
| 25-30 | የንባብ ስራ ቦታ |
| 45-50 | የቃል ጥናት እና የማንበብና መጻፍ ጣቢያዎች |
| 40-45 | የጽሑፍ ስራ ቦታ |
| 15 | እረፍት |
| 30 | ምሳ |
| 10 | የማንጸባረቅ/የሂደት ግዜ |
| 55 | የሒሳብ ስራ ቦታ |
| 60 | ልዩ ልዩ |
| 15 | እረፍት |
| 40 | ሳይንስ/ማሕበራዊ ጥናቶች/ጤና |
| 25 | የምርጫ ሰዓት |
| 10 | የትምህርት ቀን ማሳለፍ/ማሰናበት |



# ከማህበረሰብ መርጃዎች ጋር መገናኘት

**የፌርፎክስ አዉራጃ ህዝባዊ ቤተ መጻሕፍቶች**
www.fairfaxcounty.gov/library
እያንዳንዱ የቤተ መፃህፍት ቅርንጫፍ የልጅዎን አይነ ህሊና እና የቅድመ ማንበብና መጻፍ ክህሎትን ለመገንባት የተነደፈ የልጆች መጽሃፍት ልዩ ክፍል አለው። በአንድ ግዜ እስከ 50 መጻህፍቶች ለሶስት ሳምንት መበደር ይቻላል። መጽሀፍቶች በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ። ለቅድመ ትምህርት ቤት እና ለትምህርት የደረሰ እድሜ ላላቸው ህጻናት በዓመቱ ውስጥ ልዩ እንቅስቃሴዎች እና የታሪክ ጊዜዎች ይቀርባሉ። በቤተመፃህፍት ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘው ወርሃዊ "Ready to Read" ጋዜጣ ለልጅዎ መጽሀፍ ለማንበብ ጥሩ ሀሳቦችን ይሰጣል።

**ፌርፎክስ አዉራጃ የመናፈሻ ቦታዎች ባለስልጣን**
www.fairfaxcounty.gov/parks
ለቅድመ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አስደሳች ትምህርቶች በ "Parktakes" መጽሔት በኦንላይን ላይ ወይም በሕዝብ ቤተመጽሐፍትዎ ውስጥ ይገኛሉ። የፌርፋክስ አዉራጃ የተለያየ መጠን ያላቸው መናፈሻ ቦታዎች አሉት። ለትናንሽ ልጆች ቤተሰቦች ልዩ ምርጫ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት መናፈሻ ቦታዎች፡-

**Clemyjontri** በአራት የውጪ "ክፍሎች" የተከፈለ ባለ ሁለት ሄክታር የመጫወቻ ሜዳ ነው። ይህ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ጨምሮ ለሁሉም ልጆች ተደራሽ ነው። የሽክርክሪት እና የሽርሽር ድንኳን አለው።

6317 Georgetown Pike, McLean, VA 22101
703-388-2807።

**Frying Pan Farm Park** የ1920ዎቹን የሚመስል እርሻ፣ እሽክርክሪት፣ የድርቆሽ ሳር ላይ ሽርሽር፣ የገጠር መደብር እና የጎብኚዎች ማእከልን ያካትታል። ልጆች የተለያዩ የእርሻ እንስሳትን እና አሮጌ የእርሻ መሳሪያዎችን ማየት ይችላሉ። የሽርሽር ጠረጴዛዎች እና የመጫወቻ ሜዳዎች ይገኛሉ።

2709 West Ox Road, Herndon, VA 20171
703-437-9101።

**የፌርፎክስ አዉራጃ የጤና ክሊኒኮች**
www.fairfaxcounty.gov/health/clinics

ክትባቶች
ወደ ሙአለ ህፃናት ለሚገቡ ህጻናት የክትባት ሰነድ ያስፈልጋል። የፌርፋክስ አዉራጃ የጤና ክፍል አስፈላጊ የትምህርት ቤት ክትባቶችን በክሊኒክ ቦታዎች ይሰጣል።

ለቦታዎች እና አስፈላጊ የትምህርት ቤት ክትባቶች ዝርዝር ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ።

የጥርስ ህክምና
አንዳንድ ቦታዎች ነህፅናት የጥርስ ሕክምና ሊሰጡ ይችላሉ፣ ቀጠሮ ያስፈልጋል።

# ለቤተሰቦች ጠቃሚ መርጃዎች

## ሕትመቶች




**ልጅዎ መማር እንዲወድ መርዳት**
www.fairfaxcounty.gov/OFC
**ላይ** "Helping Your Child Love to Learn" **ብለዉ ይፈልጉ።**

**ከልደት ቀን እስከ** 5 **ዓመት ዕድሜ ድረስ ስለ ቅድመ ልጅነት እድገት ይወቁ። በሳይንስ፣ በሒሳብ፣ በመፃፍና ማንበብ፣ በቋንቋ፣ በፈጠራ ጥበባት፣ በማህበራዊ እና በስሜታዊ እድገት እና በጤና እና አካላዊ እድገት ላይ እድገትን ለማበረታታት ቤተሰቦች እና አስተማሪዎች ማስተዋወቅ የሚችሏቸውን ተግባራት ይፈልጉ። በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።**

**የፌርፋክስ አዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች የተሚጋች ወላጆች መመሪያ መጽሐፍ፡ ለሙአለ ሕህፃናት መዘጋጀት**
www.fcps.edu
**ላይ** "Getting Ready for Kindergarten" **ብለዉ ይፈልጉ።**

**የልጅዎ የመጀመሪያ አስተማሪ እንደመሆንዎ መጠን ለመዋዕለ ሕፃናት እንዲዘጋጁ ያግዛሉ። በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።**

## ድህረ ገፆች

**የፌርፎክስ አዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቢቶች የሙአለ ህፃናት ምዝገባ**
www.fcps.edu/registration/kindergarten registration

**የሙአለ ህፃናቱ የምዝገባ ገጽ ወላጆች የተማሪ ምዝገባን ባለ** 5-**ደረጃ ሂደት እንዲያጠናቅቁ የሚረዳ መረጃ አለው። የ** FCPS **ድህረ ገጾች በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ።**

**የፌርፋክስ አዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ሙአለ ህፃናት**
www.fcps.edu/academics/elementary-school-academics-k-6/kindergarten

**ይህ ድህረ-ገጽ ስለ** FCPS **ሙአለ ህፃናት ልምድ መረጃ አለው። ለጥያቄዎች ወደ** 703-204-6734 **ይደዉሉ ወይም ወደ** RegistrationQuestions@fcps.edu **ኢ-ሜይል ይላኩ።**

**Helping Children Learn Newsletter**
www.fcps.edu

**ላይ** "Helping Children Learn Newsletter" **ብለዉ ይፈልጉ።**

Helping Children Learn **ጋዜጣ ልጆች በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ ለቤተሰቦች ሀሳቦች አሉት።**

Daily Learning Planner **ቤተሰቦች ልጆች ለትምህርት ቤት እንዲዘጋጁ ለመርዳት በየቀኑ ሊጠቀሙበት የሚችሉት አዲስ ሃሳብ አለው።**

## ቪድዮዎች


**A Closer Look at School Readiness (የትምህርት ቤት ዝግጁነት ጠለቅ ያለ እይታ)**
www.youtube.com/watch?v=LjPK53Gfo9Y

**የተሳካ ሽግግር የሚከሰተው ቤተሰቦች፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰራተኞች እና የቅድመ ልጅነት ጊዜ አስተማሪዎች እያንዳንዱን ልጅ ለመርዳት ሲሰባሰቡ ነው።**




**የፌርፋክስ አዉራጃ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ወደ ሙአለ ህፃናት እንኳን ደህና መጡ ይላል**
https://youtu.be/YxFAwy3Uj2g

**ይህ ቪዲዮ የ**FCPS **ሙአለ ህፃናት ፕሮግራም አጠቃላይ እይታን ይሰጣል።**




## መተግበርያዎች

**Vroom**
www.vroom.org

**የ**Vroom **የአእምሮ ግንባታ ምክሮች ልጆች በትምህርት ቤት እና ከዚያም በኋላ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎቶች እንዲማሩ እና እንዲያዳብሩ ለመርዳት ለቤተሰቦች እና የመጀመሪያ አስተማሪዎች አስደሳች መንገድ ናቸው። ይህ ነፃ መተግበርያ በ** iOS **እና አንድሮይድ መሳሪያዎች (ኮምፒተሮች፣ ታብሌቶች፣ ስማርትፎኖች) ላይ ይገኛል። መተግበርያዉ በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ ይገኛል።**

**CDC Milestone Tracker የሞባይል መተግበርያ**
www.cdc.gov
Milestone Tracker **ብለዉ ይፈልጉ**

**የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል** Milestone Tracker **የልጅዎን እድገት ለመከታተል ይረዳዎታል። ከ** 2 **ወር እስከ** 5 **ዓመት ዕድሜ ያላቸው የህጻናት እድገትን ለመደገፍ ሀሳቦችን ያካትታል። ይህ ነፃ መተግበርያ በ** iOS **እና አንድሮይድ መሳርያዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች ይገኛል።**

# ለሙአለ ህፃናት ለመመዝገብ ጊዜው አሁን ነው!



**是註冊就讀幼稚園的時候了！**
如果您的孩子將於 9 月 30 日前年滿 5 週歲，請聯絡您附近的小學，以了解相關入學資訊並取得註冊資料袋.

**유치원에 등록하실 때입니다!**
귀하의 자녀가 9월 30일 이전에 만 5세가 된다면 지금 주변의 초등학교에 연락하시어 학교 정보 및 등록 서류에 대해 알아보십시오.

**Đã đến lúc để đăng ký cho lớp mẫu giáo!**
Khi con em quý vị được 5 tuổi vào ngày 30 tháng 9, thì đây là thời điểm thích hợp để quý vị liên lạc với trường tiểu học gần khu vực của quý vị để biết thêm thông tin và hồ sơ ghi danh.

If your child will be 5 years old by September 30, now is the time to contact your neighborhood elementary school for information and the registration packet.

**Ha llegado el momento de inscribirse para Kindergarten!** Si su hijo va a tener 5 años el 30 de setiembre próximo, ahora es el momento de ponerse en contacto con la escuela primaria de su vecindario para obtener información y el paquete de inscripción.

**”زمان ثبت نام برای مهد کودک است !“**
اگر فرزند شما تا 30 سپتامبر، 5 ساله می شود، زمان آن است که با دبستان محل خود تماس بگیرید تا اطلاعات مورد نیاز و بسته ثبت نام را دریافت کنید.

**”یہ کنڈرگارٹن میں اندراج کرانے کا وقت ہے !“**
اگر 30 ستمبر تک یا اس سے قبل آپ کے بچے کی عمر 5 سال ہو رہی ہے، تو وقت آگیا ہے کہ آپ اپنے علاقے کے اسکول سے رابطہ کریں اور معلومات اور داخلے کی تفصیلات طلب کریں

**”لقد حان الوقت للتسجيل في رياض الأطفال“**
إذا كان طفلك سيبلغ عمر 5 سنوات بحلول 30 سبتمبر، فقد حان الآن وقت الاتصال بالمدرسة الابتدائية القريبة للحصول على المزيد من المعلومات وحزمة التسجيل الخاصة بها.

**እንዴት እንደሆነ ይወቁ፡-**

**http://boundary.fcps.edu/boundary**


Fairfax County
OFC Office for Children
www.fairfaxcounty.gov/OFC
Amharic